


# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ
# Ethiopian Civil Service University

BUILDING CAPACITIES IN THE PUBLIC SERVICE

Est.1995

***Public Relations Directorate***

Monthly Newsletter
November 2016
Vol.13 No.4


## ቆይታ ከፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ ጋር

በቅርቡ ወደ ዩኒቨርሲቲያችን በፕሬዚዳንትነት የተመደቡት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ ከዩኒቨርሲቲው ልዩ ልዩ ዘርፎች እና የስራ ሀላፊዎች ጋር ትውውቅ በማድረግ ወደ ስራ መግባታቸው ይታወቃል፡፡ ፕሮፌሰር ፍቅሬ በዲላ ዩኒቨርሲቲ ከመምህርነት እስከ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንትነት ያገለገሉ ሲሆን ወደ ዩኒቨርሲቲያችን ከመደባቸው በፊት በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት በመሆን አገልግለዋል፡፡ በዚህ ወር እትማችን ከዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጋር ለማስተዋወቅ ቃለ መጠይቅ አድርገንላቸዋል ተከታተሉን፡፡

**ህ/ግ/ዳ፡-** በመጀመሪያ ለቃለ ምልልሱ ፍቃደኛ ስለሆኑ እናመሰግናለን

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

**ህ/ግ/ዳ፡-** በመጀመሪያ ስለ ግል ህይወትዎ እንነጋገር፡፡ የት ተወልደው አደጉ፣ የትምህርት ቆይታዎ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ የትተማሩ? በስራ ያሳለፉባቸው ተቋማት እነማን ናቸው?



**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ተወልጄ ያደኩት አረካ በምትባል በወላይታ ዞን ውስጥ በምትገኝ የወረዳ ከተማ ነው፡፡የተወለድኩትም 1960 ዓ ም ሲሆን እዚያው በተወለድኩበት አካባቢ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያ፣ መለስተኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴንም የተከታትያለሁ፡፡ በወቅቱ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ፈተና ለዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት አስመዝግቤም ስለነበር በትምህርት ሚኒስቴር በአዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአራት ኪሎ ካምፓስ በባዮሎጂ ትምህርት ክፍል ውስጥ ተመድቤ የመጀመሪያ ዲግሪዬን ተቀብያለሁ፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርቴን ካጠናቀቅሁ በኋላም በአዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዕፅዋት ቤተ መዘክር ውስጥ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመምህርነት ለሁለት ዓመታትአገልግያለሁ፡፡ በመቀጠልም ወደ አዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመመለስ በዕፅዋት ሳይንስ ስፔሻላይዝድ በማድረግ በማስትሬት ከተመረኩ በኋላ በወጣው ክፍት የስራ ማስታወቂያ ተወዳድሬ በዲላ ዩኒቨርሲቲ ተቀጥሬ በሌክቸረርነተና የኮሌጅ ሬጅስትራር በመሆን ለሶስት አመታት አገልግያለሁ፡፡

ከዚያም የኢትዮጵያና የኖርዌይ መንግስታት ባላቸው የትብብር ስምምነት መሰረት ለፒ ኤች ዲ ትምህርት ወደ ኖርዌይ አስሎ ዩኒቨርሲቲ በመሄድ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጣምራ በሚሰጠው የትምህርት ፕሮግራም ትምህርቴን በመከታተል የዶክተሬት ዲግሪዬን ተቀብያለሁ፡፡ ተርሚናል ዲግሪ ከሰራሁ በኋላም ወደ ዲላ ዩኒቨርሲቲ በመመለስ ቀድሞ በሬጅስትራርነት ሳገለግል ስለነበር ስለአካዳሚክና ደንቦች ካለኝ ተሞክሮ የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክና ምርምር ምክትል ፕሬዚደንት በመሆን ለአምስት አመታት በኃላፊነት አገልግያለሁ፡፡ ከዚህኃላፊነት በተጨማሪም ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች የተለያዩ ኮርሶችን እሰጥ ነበር፤በምርምር ስራቸውም አማክር ነበረ ፡፡ በግሌም የተለያዩ ምርምሮችን አደርግ ነበር፡፡ በወቅቱ ባስመዘገብኩትና ባሳተምኩት የምርምር ውጤት፤ ላበረከትኩት አገልግሎት፤ በዩኒቨርሲቲው ጉዳዮችም ላይ ላበረከትኩት አስተዋፅኦ ከረዳት ፕሮፌሰርነት ወደ የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ደረጃ ለመድረስ ችያለሁ፡፡

## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## Our Mission

Enhancing the service orientation , transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education, Training, Consultancy, Research and Community Services.

## Our Values

- Customer Focus
- Commitment
- Continuous Learning
- Welcoming Diversity
- Attention to the Disadvantaged
- Participatory leadership
- Collaboration

በዲላ ዩኒቨርሲቲ ባበረከትኩት አስተዋፅኦ መነሻነት ወደ ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ተዛውሬ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲም ለአምስት ዓመታት በአካዳሚክና ምርምር ምክትል ፕሬዚደንትነት አገልግያለሁ ፡፡ ከዚያም ኃላፊነት በተጨማሪም ፕሮጀክቶችን በመንደፍ፤ አንዳንድ አጋር አካላትን በማግኘት የምርምር ስራዎችን እሰራ ነበርተ፤ማሪዎችንም አማክር ነበር፡፡ በተለያዩ የማህበረሰብ ጉዳዮች፤ በአካባቢያዊ ልማት እንዲሁም ባሳተምኳቸው የምርምር ውጤቶች መነሻነት የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ ከሀዋሳ ዩኒቨረርሲቲ የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማእረግን ተቀብያለሁ፡፡

ሀ/ድ/ዳ ስለ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሚያውቋቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? ወደ ዩኒቨርሲቲው መመደብዎን ሲሰሙ ምን ተሰማዎት? እዚህ ከደረሱ በኋላ ስለ የኒቨርሲቲው የሰሙት እና በተጨባጭ ያገኙት ምን ያህል ተጣጥመው አገኟቸው?

ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡- የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲን በኮሌጅ ደረጃ ሲቋቋም ጀምሮ አውቀዋለሁ፡፡በወቅቱ ከነበሩት ኮሌጆች ሁሉ በተለየ ሁኔታ ለምን ዓላማ እንደተቋቋመ የጠለቀ ግንዛቤው ግን አልነበረኝም ፡፡በመጀመሪያዎቹ አመታት አብሮ አደግ ጓደኞቼም ሆኑ የስራ ባልደረቦቼ ወደእዚህ ኮሌጅ ገብተው ስለነበረ ከእነሱ በማገኘው መረጃ መሰረት ኮሌጁ ከሌሎች ኮሌጆች በአንዳንድ ሁኔታው እንደሚለይ ግንዛቤው ነበረኝ፡፡ ለምሳሌ እንደሌሎች ኮሌጆች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎችን በቀጥታ የሚቀበል ሳይሆን በስራ ላይ ያሉ ሰራተኞችን የሚቀበል መሆኑና የቅበላ መስፈርቱም ልዩ እንደሆነ ፤ ውስጥ ገብቶም የትምህርት አሰጣጡና የምዘና ስርዓቱ ከሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቀቋማት በተለየ መልኩ እንደሚፈጸም ፤የመምህራንና ተማሪዎች ግንኙነት፤ የተማሪ ለተማሪ ግንኙነት ከሀገራችን የተለመደወ ሁኔታ የተለየና መልካም የሚባል መሆኑን አውቅ ነበር፡፡

በመቀጠልም ከዚህ ተቋም ተመርቀው የሚወጡ ሰልጣኞች በሀገር ደረጃ እያሳደሩ ያለው ተፅዕኖ ከፍ እያለ ሲመጣ ዩኒቨርሲቲው በርካታ ጉዳዮች በፖለቲካው ፤ ኢኮኖሚውም ፤ በአመራር ደረጃም ተጽዕኖ ፈጣሪ ተቋም እንደሆነ ለመታዘብ ችያለሁ፡፡ በክልልም ሆነ በፌደራል ደረጃ ሀገሪቷን እየለወጡ አሁን ካለችበት ደረጃ ያደረሱ አመራሮች በአብዛኛው ከዚህ ዩኒቨርስቲ የወጡ መሆናቸውን ነው የተገነዘብኩት ፡፡መንግስት ካለሁበት አመራር ቦታ ወደዚህ ዩኒቨርሲቲ ምደባ ሲሰጠኝም ትልቅ አጋጣሚ አድርጌ ነው ያየሁት ፡፡ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀላል ስላልሆነና የዚህ አስተዋጽኦ አካል መሆኔ በራሱ ለእኔ ትልቅ እድል አድርጌ ነው የምወስደው ነው፡፡

አዳዲስ ነገሮችን ማወቅ ፤ተግዳሮቶችን መጋፈጥ የእኔ የህይወት መርህ ነው፡፡ ስለዚህ ወደ እዚህ ስመጣ አዳዲስ ነገሮችን ለመማርና ለማወቅ እንዲሁም ከለሎች ጋር ለአንድ አላማ መንቀሳቀስ የሚል ተልዕኮን አንግቤ ነው፡፡ ከውጪ የሰማሁትና አሁን በማየው ነገር መካከል እምብዛም የተለየ ነገር የለም ፡፡ እንደ ሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰራ የአስተዳደር ስርዓት ነው ያለው፡፡ በእርግጥ ከመጣሁ ጀምሮ በሂደት ዝርዝር ነገሮችን ለማነጻጸር ጊዜው አጭር ቢሆንም እስካሁን ግን ምንም ያየሁት የተለየ ነገር የለም ፡፡

ሀ/ግ/ዳ በአጋጣሚ እርስዎ የደረሱት ዩኒቨርሲቲው አዲስ መዋቅር ሰርቶ ወደ ድልድል ለመግባት በዝግጅት ላይ እያለ ነው፡፡ ይህ አጋጣሚ ለስራዎ ይፈጥራል ብለው የሚያስቡት መልካም ነገር ካለ ቢገልጹልን?

ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-ለአንድ ተቋም የሰው ኃይሉ እጅግ በጣም ወሳኝ እና እንደ ቁልፍ ግብዐትም ተደርጎም ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ በተለይ በፋይናንስ፤ በፋሲሊቲ፤ በንብረት እያያዝ ወዘተ በሚሰጠው አጋልግሎትና ካለው ድርሻ አንጻር የሰው ኃይል ትልቁ ቁልፍ ነው፡፡ ስለዚህ አሳሪ የሆነው መዋቅር ተሻሽሎ በአዲስ መልክ ተዘጋጅቶ የሰው ኃይል ድልደላ እየተካሄደ ባለበት ወቅት በመምጣቴ እድለኛ ነኝ ብዬ ነው የማስበው፡፡ ምክንያቱም አንድ ተቋም ሊለወጥ ፤ ሊሻሻል ተልዕኮውን በአግባቡ ሊፈጽም የሚችለው በተለይ የሰው ኃይሉ በእውቀትና በክህሎት የዳበረ ስራተኛ ይዞ ሲንቀሳቀስ ነው፡፡ ስለዚህ አሁን የተጀመረው የሰው ኃይል መዋቅር የድልድል ስራ በአፋጣኝ መፈጸም አለበት፡፡ ውስጥ ያሉትን ሰራተኞችን በመዋቅሩ ደልድሎ የሚቀሩ ክፍት ቦታዎች ላይ ደግሞ በቅጥር የሰው ሃይሉን አሟልቶ መንቀሳቀስ ውጤታማና ጠንካራ ተቋም ሆኖ ለመዝለቅ የሚያግዝ ተግባር ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ መምጣቴ እድለኛ ነኝ ነው የምለው እንጂ እንደ እንቅፋት አድርጌ አልወሰደውም ፡፡

ሀ/ግ/ዳ የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ከሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አንጻር የተሰጠው ተልእኮ ለየት ያለ እና የቅበላ ስርአቱም የተለየ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ለስራዎ እንደ መልካም አጋጣሚ እና እንደ ተግዳሮት ሊያመጣ የሚችለው ነገር ይኖ ርይሆን?

ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡- ዩኒቨርስቲው ከተሰጠው ተልዕኮ አንጻር በሀገሪቱ ያለውን የሲቪል ሰርቪስ ሴክተሩን አቅም መገንባት ከሚለው ስነሳ የሲቪል ሰርቪሱ እንደ ሀገር የአንበሳውን ድርሻ የሚወስድ ሴክተር ነው፡፡ ስለዚህ የዚህን ኃይል አቅም መገንባት እንደ ተልዕኮ ስመለከተውና በሀገሪቱ ያለው ብቸኛ ተቋም መሆኑን፤ ተልዕኮው ጥልቅ መሆኑን ሳስበው እለት ተዕለት ተግቶ መስራትና ውጤታማ ሆኖ መገኘትን፤ አስቸጋሪና ብርቱ ጥረት የሚጠይቅ እንደሚሆንም አያጠራጥርም፡፡ የሆነ ሆኖ ግን ከዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ጋር ተባብረን እንደ አንድ ሰራዊት ከተንቀሳቀስን ይህን እንደምናሳካው አምናለሁ ፡፡ከዚህ ባሻገር የቅበላ ስርዓቱ መለየቱ መንግስት እንደ አሰራር ያስቀመጠው ስልሆነ በአሰራሩ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ምናልባት የሰለጠኑ ሲቪል ሰርቫንቶች ቁጥር ሲያድግና አቅማቸውም በበቂ ሁኔታ እየተገነባ ሲመጣ መንግስት የተለየ አካሄድ ሊከተል ይችላል፡፡ በዚያን ጊዜ ደግሞ የቅበላው ሁኔታም እየተቀየረና እየተሻሻለ የሚሄድበት አቅጣጫ ከመንግስት በኩል ይሰጣል የሚል ሀሳብ አለኝ ፡፡

ቀድሞ በነበርኩበት ዩኒቨርስቲና በዚህ ዩኒቨርስቲ መካከል ያለው ልዩነት በተመለከተም በቅበላውና በሌሎች ነገሮች መለየቱ በስራዬ ላይ ብዙ ተግዳሮት ችግር ይኖረዋል የሚል እምነት የለኝም፡፡

**ህ/ግ/ዳ** ወደ ግል ጉዳይዎ እንግባና ከሰው ጋር በሚኖርዎ ግንኙነት የሚስደስትዎት ነገር ምንድን ነው? የሚያስከፋዎትስ ነገር?

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** በሰብዐዊ ፍጡርነት የሰው ልጅ ትልቁ ብስለትና ስኬትም የሚለካው ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት ነው፡፡ በእኔ እምነት ሰዎቸ ከሰዎቸ ጋር የላቸውን ግንኙነት በአግባቡ ማስኬድና ማስተናገድ መቻላቸው እንዲሁም አሉታዊ ነገሮችን ለመቋቋም መቻል ለአንድ ሰው ብስለት ትልቁ መለኪያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡በተለይ ኃላፊ የሆነ ሰው የሚመራውና ስራውንም የሚያከናውነው የተለያየ አመለካከት፤ ፍላጎትና የራስ የሆኑ ነገሮችን ከያዘ ሰው ጋር ነው ፡፡

ስለዚህ የሚያስደስተኝና ቢዋጣልኝ የምለው ከውስጥ ሰራተኞችም ሆነ ከውጪ የሚመጡ አካላት ጋር ያለኝ ግንኙት ከአድሎ የጸዳና ውጤታማ አገልግሎትን መስጠት፣ በቅንነት ለማገልገል መትጋት ነው፡፡ በዚህ ውጪ ደግሞ በአሉታዊነት አስመሳይነት፣ በስራ መለገም፣ ወገንተኝነት ከመሳሰሉ ነገሮች አብረውኝ የሚሰሩ ሰዎች ቢጸዱ ደስ ይለኛል፡፡ በእኔ ላይ ሊደርስ የማልፈልገውን ነገር በሌሎች እንዲደርስ አልፈልግም ፡፡ እኔን የሚያስደስተኝ ሰዎች እኔ በምሰጠው አገልግሎት እንዲረኩ እና የተቻለኝን ጥረት አድርጌ ውጤታማ ሆኖ መገኘት፣ ተቋሙም አላማውን አሳክቶ ስራው ውጤታማ ሲሆን ማየት ነው ፡፡ በዚህ ግኑኘት ደግሞ ከሰዎች ጋር በጋራ በተቻለኝ መጠን አዎንታዊ የሆነ ማንንም ቅር የማያሰኝ እና ከአድልኦ ወይም ከመሳሰሉት ነገሮች በጸዳ ሁኔታ ለማገልገል በማደርገው ጥረት ሌሎች ሰዎችም በዚሁ አይነት መልኩ እንዲተጉ ነው ውስጤ የሚመኘው፡፡ የሚያስመስል ሰው፣ በስራ የሚለግም ሰው ፣ በወገንተኝነትና በዘመድ አዝማድ የሚሰራና አላስፈላጊ በሆነ መንገድ ለመጥቀም የሚጥር ሰው ሳይ እርሱ ያስከፋኛል፡፡

**ህ/ግ/ዳ** መቼም የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትነት ስራ ጫናው ከፍ ያለ ነው? ሆኖም ባለችዎት ትርፍ ጊዜ የሚያዘወትሩት ነገር ምንድን ነው?

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ትርፍ የሚባል ጊዜ አለ ብዬ አላምንም፡፡ በግሌ ሁለት ኃላፊቶችአሉብኝ፡፡ የመንግስት ኃላፊነት በአንድ በኩል ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቤተሰብ ኃላፊነት አለብኝ፡፡ትርፍ ጊዜ ሳገኝ ደስ የሚለኝ ያንን ጊዜ ለቤተሰቤ ሳውለው ነው፡፡ ልጆቼን በትምህርታቸው ባግዛቸው ፤ ከእነርሱ ጋር ለራሴም ለእነርሱም አዕምሮ የሚያስደስት ነገር ማከናወን ነው የሚያስደስተኝ፡፡ በመጀመሪያ ቤተሰቡን በአግባቡ ያልመራ ሰው የሚመራው ተቋምም፣ በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮችም ውጤታማ ሊሆን ስለማይችል እና ሁሉም ነገር ከቤተሰብ ስለሚጀምር ጊዜ ሲኖረኝ ለዚያ የቤተሰብ ኃላፊነቴ ነው የማውለው፡፡ ከዚያ ያለፈ ጊዜ ሲኖረኝ ደግሞ አንዳንድ ከትምህርትና ከስራዬ ጋር የተያያዙ፣ ከምርምሬም ጋር የሚያያዙ ነገሮች ላይ ነው የማሳልፈው፡፡

**ህ/ግ/ዳ** በኢ.ሲ.ሰ.ዩ. ቆይታዎ የኒቨርሲቲውን የት ላይ ማድረስ ይፈልጋሉ? ለዚህስ ከዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ምን ይጠብቃሉ?

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ተቋሙ የተሰጠው ተልዕኮ ግልጽ ነው፡፡ በሀገሪቱ የሲቪለ ሰርቪሱን ችግር እየለየ በትምህርት ፣ በስልጠናና በማማከር አቅምን የመገንባት ተልዕኮውን በመወጣት ላይ ነው ያለው፡፡ያንን በጥልቀትና በስፋት ለማስኬድ ነው የማስበው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ዩኒቨርስቲውለወደፊት ታላቅ ርዕይ አስቀምጧል፡፡ በሀገር ደረጃ ከሚያሳርፈው ተጽዕኖ አልፎ ወደ ምስራቅ አፍሪካ አና በአጠቃላይ በአፍሪካም የልቀት ማዕከል ለመሆን ርዕይ አለው፡፡ስለዚህ አሁንይህን ትልቅ ርዕይ በተቀመጠው ጊዜ በ2025 እንዴት ወደዚህ ደረጃ መውሰድ እችላለሁ ብዬ ነው እያሰብኩ የለሁት፡፡ እንደ መጀመሪያ የማስበው የአካዳሚኩ ዘርፍን ወደዚህ የልቀት ማዕከልነት ማምጣት፤ አሁን እየተሰጡ ያሉትን ፕሮግራሞች በተለይ በጥናት ላይ ተመስርቶ ጥራት ያላቸው እንዲሆኑ ማድረግ ፤ ጥልቀት ያለው የስልጠና ፕሮግራሞች እንዲሆኑ ማድረግ ነው ፡፡ ስለዚህ አዳዲስ ፕሮግራሞችና ስርዓተ ትምህርት ቀርጸን ይህን የሚተገብሩ ብቁ እና በቂ የመምህራን አቅም መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ስለዚህ በመምህራን ልማት ላይ የሚሰሩ ስራዎች ይኖራሉ፡፡ ፕሮግራሞችንም በጥናትላይ የተመሰረቱ ፣ በሀገራችን የሲቪል ሰርቪሰ ሴክተር ችግሮች ላይ ያነጣጠሩ፣እንዲሆኑና ከዚያም አልፈው በተመሳሳይ በምስራቅ አፍሪካና በአህጉር ደረጃም እንዲሁ ስፋትና ጥልቀት ኖሮት በተገቢው ሁኔታ እንዲሰጡ ለማድረግ ነው፡፡ በምርምርም እንዲሁ ጥልቅተ እንዲኖረው፤ ማማከርም ችግር ፈቺ ሆኖ እንዲሰራ ደረጃውን የጠበቀለማድረግ ነው የታሰበው ፡፡ የአሰለጣኞቹ አቅም መገንባት አለበት፡፡ የሚሰጡሞጁሎችና የትምህርት ማቴሪያሎች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው፡፡ ስለዚህ ስልጠናው ሲቪል ሰረቫንቱን ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራትም መጥተው የሚሰለጥኑበት ማዕከል የማድረግ ርዕይነው የተያዘው፡፡ ከዚህ ጋር በእኩል ደረጃ ተያይዞ መሄድ ያለበት በዩኒቨርስቲው ያለው መሰረተ ልማት፣ የህንጻ ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማዕከል፣ የቤተ መጻህፍትና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ አካላት አጠቃላይ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ክፍሎችን በማዘመን የተሻለ ቁመና ላይ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ሰራተኛውም በዚያ ደረጃ አቅሙ እየተገነባ መሄድ አለበት ፡፡ በአጠቃላይ ልዩ ተኣምር መፍጠር ሳይሆን አድማሱን፣ ስፋቱና ጥልቀቱ እየሰፋ የሰው ኃይሉና ግብዐቶችም በዚያ ደረጃ እየተሟሉ የሚሄድ ተቋም አድርጎ የማውጣት ተግባር ነውና በየዘርፉ ከዓመት ዓመት ተጨማሪ ለውጥ እያመጣን ወደዚያ የልቀት ማዕከልነት ለመምጣት ነው የማስበው፡፡ በዓጠቃላይ የየኒቨርሲቲውን ራዕይና ተልዕኮውን ለማሳካት የአመራር ሚናዬን መጫወት ነው ፡፡

**ህ/ግ/ዳ** .በመጨረሻ ቀረ የሚሉት ነገር ካለ እና ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥዎ?

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ለዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ የማስተላልፈው መልዕክት የምናገለግለው ሀገራቸንን ነው፡፡ የሌላ ሰው ሀገርን አይደለም፡፡ ለሀገራችንም የእኛን አግልግሎት ማበርከት እንደዜጋ ከእኛ ይጠበቃል፡፡ስለዚህ ሁሉም የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ አካላት፣ መምህራን፣ ሰራተኞች፣ አሰልጣኞች በየተሰማራንበት መስክ ለሀገራችን እድገትና ህዳሴ ብርቱ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡ሀገራችን ስትለወጥ የእኛም ህይወት ይለወጣ፡፡ የልጆቻችንም የወደፊት ዕጣ ፈንታ አሁን እኛ በምናደርገው ነገር ላይ ነው የሚወሰነው፡፡ ስለዚህ ለማንም ተብሎ ሳይሆን የሚሰራው ለጋራ ሀገራዊ ለውጥ ነው፡፡ስለዚህ ይህን ትልቁን ማዕቀፍ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሁሉም መንቀሳቀስ አለበት፡፡ እዚህ ጋር አለቃ፣ ሀላፊ ፣ሰራተኛ የሚባል ነገር የለም፡፡ሁላችንም በየድርሻችን ለሃገራችን እድገት መጣር አለብን ፡፡ ውጤቱም ፣ ለውጡም የጋራችን ነው፡፡በተሳተፍነው ልክ ደግሞ የምንጠቀምበት ነውየሚሆነውና ጠንክረን እንድንሰራ በህብረት እንድንቀሳቀስ በዚህ አጋጣሚ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡

## The Eleven Nations, Nationalities and Peoples Day Celebrated at ECSU

Ethiopian Civil Service University and Ministry of Public Service and Human Resource Development jointly celebrated 11th Nations, Nationalities and Peoples day on 01 December 2016 at Abay Hall. The day was celebrated with a theme“Constitution in our Democratic Unity for our Renaissance”.



In his opining speech Ato Tagesse Chaffo, minister for Ministry of Public Service and Human Resource Development said since the endorsement of the constitution, many tangible and objective changes have been registered in our country. People with different ethnic background are now living in harmony. For this, our constitution served as a basic foundation of our peace and stability.It is also a covenant for people self rule and administration. This is a special day that our people endorse the constitution with full willingness and commitment. It is also aday that we express our respect and loyalty to our constitution and stand together for our country’s renaissance, he added.

Ato Tagesse Chaffo also stated that some anti peace elements are now working hard to destabilize





our country's peace and stability by abusing our people’s requests for good governance and equal opportunity from the economic development. The federal government has given a due attention to solve these problems.The civil servants must also play their important role to ensure the benefit of our people, guarantee good governance, fairness and transparency for our nation. When we celebrate this day, we have to prepare ourselves for the great responsibility to accomplish our mission in the future, AtoTagesse Chaffo underscored.



On the program two papers entitled“ Constitution to Build a Democratic State and Democratic Institutions” and “Multi Nationalism for Building a Common State” were presented by scholars and house discussed on the issues raised by presenters.



On the occasion different Nations, Nationalities traditional songs were presented to the audience.

## The New President Holds Discussion with Staff

The newly appointed president of Ethiopian Civil Service University, Professor Fikre Dessalegn, has been holding an introductory meeting with the University community. Professor Fikre met with the academic wing directors on November 16, 2016. He also met with the management support services directors and research and community services directors on November 17, 2016.



During the meetings, he said he is honored to be part of the University. He also applauded the University`s contribution in the country`s social, economic and political achievements. The contribution of the graduates of the University is felt in every sector as most of them are the main actors from the lower tier of the government to ministerial level. You should be proud of this, because it is you who shape







their attitudes to become public servant he underscored.

In the occasion Professor Fikre raised curiosity questions which he believed that they will give him a glimpse of how the University is working. The questions included, among others, students` admission, modularization, instructors` class management, course offerings, expatriate staff period allotment, the new structure and research and community services. Professor Samson Kassahun and Ato Birhanu Belayneh with their team had given brief explanations on the issues.

Professor Samson in the occasion explained the journey of the University since its establishment. “When the University started as a college, it was organized in faculty. To meet the growing demands of the public sectors, a need arise to reorganize the faculties in institutes," said Professor Samson. Regarding the student instructor ratio, it is one instructor to twenty students, which is well in the ideal level. He also said that some institutes like Institute of tax and Customs Administration, Institute of Leadership and Good Governance and School of Diplomacy and International Relations are opened following the requests of federal ministries.

Ato Birhanu Belayneh also explained the core works of research and community services and the overall structure.

Professor Fikre finally stressed on the need to exert concerted efforts to achieve the vision of the University- to become a leading center of excellence in public sector capacity building in Africa by 2025. To achieve this, we need to examine the organizational structure, staff profile, research capacity, facility, IT infrastructure, library of the university which are believed to excel in the areas, said in conclusion.

## ECSU College of Urban Development and CUMTTC Hold Workshop

Ethiopian Civil service University College of Urban Development together with Centre for Urban Management and Transformation Training and Consultancy in collaboration with Farm Africa and Mercy Corps Ethiopia held a one day stakeholders discussion workshop on Green-Urban Planning and Management on 30 November 2016 at ECSU Hidasse Hall.





On his opening speech Dr. Daniel Lerebo, Director for College of Urban Development and Engineering welcomed all the stakeholders and the participants of the workshop. He also said this workshop is essential to combat the challenges of climate change and lead us in the right path. Representatives of Farm Africa and Mercy Corps Ethiopia on their part expressed their pleasure to have discussion with the stakeholders.





The workshop is organized with the objective to strengthen Green- Urban planning and Management to improve the resilience of urban systems to climate change in seven municipalitiesArbaminich andJinka, from SNNPR, Semera and Awash from Afar region and Kebridehar , Degehabour and Gode from Somali region. On the workshop the preliminary findings of the research conductedon the seven municipalities and proposals for each of the targeted municipalities to strengthen their respective capacity in Green –Urban planning, implementation and management were presented in two sessions by the research team. The thematic areas of the research were focused on geological and climate condition, waste management practice and green infrastructure development.

On the workshop it is pointed out that little attention is given to Green Urban planning and development and it is not going in a good way. Lack of green and clean development activities, lack of awareness of green and clean town development,lack of materials and man power for green and clean town development as well as poor soil quality and water supply in some areas were stated as challenges for Green-Urban development. It is also known from the research findingsthat in the targeted municipalities less attention is given to parks, open space in residential areas, sports fields and facilities. The researchers also presented a project proposal for each of the towns to alleviate these problems and recommended community participation and active involvement of all the stakeholders.

Finally the participants held discussions on the points raised and the preliminary results of the research.

We have learnt that Ethiopian Civil Service University, Farm Africa and Mercy Corps Ethiopia signed memorandum of understanding on working in partnership, coordination and collaboration to achieve the objective of strengthening Green-Urban Planning and Management.

## Research Proposal Writing Training Given

Ethiopian Civil Service University Centre for Cross - Cutting Issues Training and Consultancy gave a half day training on research proposal writing for 2009 E.C academic year prospective female graduating students on 11 November 2016, at ECSU training room.



On her opening speech W/ro Abay Akemachew Director for Centre for Cross- Cutting Issue Training and Consultancy said the center is working hard to empower female students in all aspects and assist them in their learning activities. By identifying the problems they may face, the center gives them training and consultancy. The center is working hard to increase the number of female students' graduation rate. With this great objective, this program is organized to help you develop your research proposal writing skill by refreshing what you have learned in the normal class learning time. We have also planned to give consecutive training on data analysis and writing techniques, how to present research papers and how to defend in research presentation in the next training programs. I hope you will attend the training attentively and develop your knowledge of research proposal preparation and writing skills, W/ro Abay Akemachew added.

Professor Melese Asfaw, Director for School of Graduate Studies voluntarily gave the training. On the training session Professor Melese presented the whole techniques and procedures that



should be taken in to account during research proposal preparation and writing. He also pointed out the effects and problems that may occur if the research proposal is not properly designed. Students on their part raised different questions and Professor Melese gave detail explanation for them.

The training was organized by Gender and Development Unit under the Centre for Cross Cutting Issue Training and Consultancy .On the training more than 120 female prospective graduating students participated.

በ2009 የትምህርት ዘመን በወራሀዊ እና  የስድስት ወር  መጽሂቶች ላይ የተለያዩ ትምህርታዊ፣ አዝናኝ እና አሰተማሪ ጽሁፎች ማቅረብ የምትፈልጉ ሁሉ በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት ጽሁፎቹን ማቅረብ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ
ኢሜል፡-pr.ecsu@gmail.com   telephone 011-646 28 87/ Ext 253/257

# The New Structure of the Academic Wing of ECSU

## Academic Vice President

College of Urban Development and Engineering (CUDE) (under this college the following departments are organized

College of Finance, Management and Development (CFMD) (under this college the following departments are organized)

College of Leadership and Governance (CLG) (under this college the following departments are organized)

### Department of Urban Planning and Development (with programs)

a. Urban planning and Development (PHD)
b. Urban and regional Studies (PHD)
c. Urban Planning and Development (MSc)
d. Urban Planning (BSc))

### Department of Urban Engineering and Surveying (with programs)

a. Urban Engineering (BSc)
b. Surveying Engineering and Mapping (BSc)

### Department of Urban Infrastructure and Transport Management (with programs)

a. Urban Mobility, Infrastructure Planning and Management (PHD)
b. Urban Transport Planning and Management (MSc)
c. Urban Infrastructure Provision and Management (MSc)

### Department of Urban Land Development and Management (with programs)

a. Urban Management (MA)
b. Urban Land Development and Management (MSc)
c. Urban Land Management and Information System (BSc)

### Department of Housing and Real Estate Property Management (with programs

a. Housing Provision and Management (MSc)
b. Property Valuation and Asset Management (MSc)

### Department of Environment and Climate Change (with programs)

a. Environment and Resilience Management (PHD)
b. Environment and Climate Change Management (MSc)

### Department of Public and Social Security Management (with programs)

a. Public Management (PHD)
b. Public Management (MA)
c. Social Security Management (MA)
d. Office Management (BA)

### Department of Development Economics and Management (with programs)

a. Development Economics (MSc)
b. Development Management (BA)

### Department of Public Financial Management and Accounting (with programs)

a. Public Financial Management (PHD)
b. Public Financial Management (MA)
c. Public Financial Management (BA)
d. Accounting and Finance (MSc)
e. Accounting and Finance (BA)

### Department of Tax and Customs Administration (with programs)

a. Customs Administration (MA)
b. Tax Administration (MA)
c. Tax and Customs Administration (BA)

### Department of Procurement and Assets Management (with programs)

a. Procurement and Assets Management (MA)
b. Procurement and Asset Management (BA)

### Department of Mathematics and Statistics

Offers common courses for all colleges

### Institute of leadership and Good Governance (with program)

a. Leadership and Good Governance (MA)

### School of Diplomacy and International Relations (with program

a. Diplomacy and International Relations (MA)

### African Institute of Governance and Development (with program

a. Governance and Development (MA)

### School of Policy Studies (with program)

a. Public Policy Studies (MA)
b. Social Policy (MA)
c. Development Policy (MA)
d. Policy Analysis (MA)

### School of law and federalism (with programs)

a. Federalism and Intergovernmental Relations (MA)
b. Comparative Public Law and Governance (LLM)
c. International Law (LLM)

### Department of English Language

Offers common course in English language for all colleges